# ያ ትውልድ

የ«ያ ትውልድ ተቋም» ልሳን

ያ ትውልድ ቅጽ 5 ቁጥር 3 የካቲት ፲፱ ቀን ፪ ሺህ ፲ ዓ.ም.


## የያ ትውልድ ድረ ገጽ

*(የካቲት 1966 ዓ.ም. 44ኛ ዓመት መታሰቢያ ምክንያት በማድረግ)*

"ፋኖ ተሰማራ . . . ፋኖ ተሰማራ፤

እንደ ሆችሚኒ እንደ ቼኩቬራ

በዱር በገደሉ ትግሉን እንድትመራ"

"አትነሳም ወይ አትነሳም ወይ፤ የግፍ አገዛዝ አይበቃህም ወይ? ተነስ . . . ተንሽ . . ."

"ተው ስማኝ ሀገሬ ኧረ ስማኝ ሀገሬ፤ ተውስማኝ ሀገሬ ሊከፋኝ ነው መኖሬ ፤ ተው ስማኝ ሀገሬ"

"ጥላሁን ለምን ለምን ሞተ?

ማርታ ለምን ለምን ሞተች?

ዋለልኝ ለምን ለምን ሞተ?፤

በትግል በሞት ነው ነፃነት የሚገኘው"

እነኚህ ዜማዎች ከነቅላጼያቸው በጊዜው ለነበርነው ትውልድ 44 ዓመት ከዕድሜያችን ቀንሰን ልጅነታችንን፣ አፍላ ወጣትነታችንና ጎልማሳነታችንን እንደ ዕድሜያችን ያመጣልናል፣ ትዝታን ይጭርብናል። ተመልሶ አይመጣም እንጂ ጊዜን ጠቅልለን ወደዚያ ዘመን ብንመለስ ይህ ቢደረግ ኖሮ እያልን ያለንን ቁጭት፣ ፀፀት፣ ፍላጎት እንዴት እንደምናስተናግደው መግለጽ አዳጋች ይሆናል።

የካቲት 1966 ሕዝባዊ አብዮት ሁለት አራቶችን ጎን ለጎን አስከትሎ አርባ አራት ዓመቱ። ያ ሀገሬን፣ ኢትዮጵያዬን፣ ሕዝቤን ያለ ትውልድ ያለምንም ጥርጣሬ ለሀገሩና ለሕዝቡ የአዲስ ስርዓት ልምላሜ ሊያይ ልዩ ምኞት የፈነጠቀበት። ለዚህ ፍጹም ለሆነ እምነቱ "የትግሉ ነው ሕይወቴ" ያለበት ዘመን። "ልጓዝ በድል ጎዳና" ያለበት ዝማሬ የደም ጐዳና ሁኖ ስንቱን ያስለቀሰበት። ለዚህ አዲስ ስርዓት ልምላሜ አጥንቱ የተከሰከሰበት፣ ደሙ የፈሰሰበት ትዝታው የሚሸሽበት፤ ፀፀት ብቻ። ጨለማ የዋጠው ቀን፣ የጨረቃ ድምቀት በደመና የተጋረደበት፣ ፀሐይ ብርድ የረጨችበት፤ ትዝታ ብቻ።

የካቲት 1966 ብሩህ ተስፋ ለኢትዮጵያ፣ ዳቦ ለተራበ፣ ፈውስ ለሕሙማን፣ የመኖር፣ የመሥራት፣ የመማር፣ የመጻፍ፣ የመናገር፣ የመሰብሰብ፣ የመደራጀት፣ የመሰለፍ፣ መንግሥት መምረጥ፣ መንግስት ማውረድ፣ ሕግ የበላይ፣ ስልጣን የሕዝብ፣ መሬት ለአራሹ፣ ሴት ከወንድ እኩል፣ ለተመጣጣኝ ሥራ ተመጣጣኝ ክፍያ፣ የሃይማኖት እኩልነት፣ የብሔር/ብሔረሰቦች እኩልነት . . . ተስፋ ሰንቆ፣ ተስፋን መግቦ፣ በትኩስ ኃይል ወጣት እጅግ የጦዘበት አብዮት።

ገኘሮና ተገኘሮ፣ በዝባዥሮና ተበዝባዥሮ፣ ባላባትና ጭሰኛ፣ አድሃሪና ተራማጅ፣ ቀኝና ግራ . . . ቃላቶች የፈሉበት። ማርክሲዝም ሌኒንዝም፣ ሶሻሊዝም፣ ካፒታሊዝም፣ ኅብረሰባዊነት፣ ኅብረሱታፊነት እኩልነት፣ አይዲያሊስት ማቴሪያሊስት፣ ገበሬ በአርሶ አደር፣ ጭሰኛ በአፈር ገፊ፣ ሠርቶ አደር በወዝ አደር/በላብ አደር . . . ቋንቋን አሳድጎ፣ በቃላት ጨዋታ ትውልድ የበላበት፣ ተስፋን የዋጠበት፤ ቀሪው ትዝታ ነው መለስ ብለው ሲያዩት።

ኢትዮጵያ ሀገራችን ከነበረችበት ኋላ ቀር ባላባታዊ ሥርዓት ተላቃ በልማትና በዕድገት ጎዳና ትራመድ ዘንድ ሁሉም ምኞቱ ቢሆን፣ አስፈጻሚውን ዕውቀትና ሕግ ፤ ድንቁርናና ጉልበት፣ መሪውን ብዕርና ወረቀት ፤ መሣሪያና ጥይት ከተኩት ለውጥ መጣ፣ መንግሥት ሄደ መሠረታዊ የሀገር ጥያቄዎች ምላሽ አያገኙምና የካቲት 66 ያነሳቸው ድህነት፣ ረሃብ፣ በሽታ፣ ድንቁርና፣ መብት እጦት፣ ዛሬም ከሕዝባችን፣ ዛሬም ከሀገራችን፣ ዛሬም ከእኛው ጋር ኗሪዎች ናቸው።

ዛሬም ከ44 ዓመት በኋላ የካቲትን ናፋቂዎች ነን። የካቲት ለምን ከሸፈ? ስንል "አለመደራጀት" አጭር መልስ ሲሆን አስተምሮን ከአለፈው ተምረን፣ እጆቿን ወደ ልጆቿ የዘረጋችውን ኢትዮጵያ አስተቃቀፍ አቅቶን ይኸው አርባ አራት ዓመት ዛሬም የካቲትን ናፋቂዎች ነን።

በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ኢትዮጵያ ዳግም የካቲትን ልታምጥ ቄሮ በኦሮምኛ፣ ፋኖ በአማርኛ እያለች ነው። ሕዝባችን ያኔ ታግሎ ያመለጠው የዜግነትና የዴሞክራሲ መብት ጥያቄ ዛሬም ከዘረኛ አገዛዝ ጋር ያስተናንቀናል። በፋሽስታዊ ወታደራዊ አገዛዝ የተቀማው የሕዝብ መንግሥት ጥያቄ ዛሬም ለነፃ ምርጫና የሕዝብ መንግሥት ምስረታ በየቦታው ይፋለማል። ያ ትውልድ በወታደራዊ አገዛዝና ካድሬዎቹ ላነገባቸው ጥያቄዎች ጥይት ተቸሮት ቢያሸልብም ጥያቄው መሠረታዊ ነውና የዛሬም ወጣቶች እየታሰሩበት፣ እየተደበደቡበት እየተገደሉበት ነው። ትላንት በ"አብዮት ጥበቃ" አፈር የለበሰ ትውልድ ዛሬ በ"ኢጋዚ ጦር" ቀጣይ ትውልድ እየተለቀመ ነው። ትላንት ኢትዮጵያዊነት ብሔራዊ ስሜት ባነገበ አምባገነን፤ ዛሬ በለየለት ዘረኛ ቡድን ሀገርና ሕዝብ ታምሰዋል። የሕዝብና የልጆቹ ጥያቄ ትላንትም ዛሬም ሀገሬ፣ ሰንደቅ ዓላማዬ፣ የዜግነት መብቴ፣ ኢትዮጵያዬ ነው።

«ያ ትውልድ ተቋም» የ60ዎቹን ትውልድ ማዕከል ያደረገ የመረጃ ማሰባሰቢያ ድረ ገጹ ዋነኛውና አንዱ ተልዕኮው ነው። ይህ ድረ ገጽ ለያ ትውልድ ፋኖዎች እንደ መታሰቢያነቱ በአሁኑ ወቅት የህወሓት/ኢሕአዴግን አገዛዝ እየተፋለማችሁና መስዋዕትነት እየከፈላችሁ ላላችሁ ተተኪ የያ ትውልድ ቤተሰብ ወጣቶችና ሌሎች የህብረተሰብ ክፍሎች ቀጣይ መታሰቢያ ይሆናችሁ ዘንድ የትላንቱን፣ የዛሬውንና የነገውን በማካተት ዘላለማዊ ድረ ገጽ እንዲሆን ተደርጎ ተዘጋጅቷል። ያ ትውልድ ያነገበውንና ለድል ያልበቃበትን ሕዝባዊ መፈክሮች ይዛችሁ ለሀገራችሁ ሉዓላዊነት፣ ለሕዝባችሁ አንድነት በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ልጆች የምታደርጉት ተጋድሎ እኛ የያ ትውልድ አባላትን ያኮራናል፣ ተኪ ትውልድም ሀገራችን አግኝታለች እንላለን። «ያ ትውልድ ተቋም» በአንድ በኩል የያ ትውልድ ቀይ ሽብርና ሌላም ሰማዕታትን በሌላ በኩል የቀይ ሽብር ፖሊሲ አውጭዎችንና ተሳታፊዎችን ዝርዝር በታሪክ ማህደሩ እንዳካተተ ሁሉ አሁን ባለው አገዛዝም 27 ዓመት ሂደት በዘር

ማጥፋትና በሌላ ሰማዕት የሆኑ ወገኖችንና የድርጊቱ ዕቅድ አውጭዎችንና ገዳዮችን ዝርዝር ለማካተት ተዘጋጅተናል።

«ያ ትውልድ ተቋም» የካቲት 44ኛ ዓመትን ስናስብ የያ ትውልድ ፈርጦችን፣ እኚያ አብሪና ተወርዋሪ ኮኮቦችን ከፍ ከፍ እያደረግን ነው። "ታሪካችሁ ህያው ነው!" ብለን የዛሬ አምስት ዓመት ተኩል ለስማችሁ መታሰቢያ ከጀመርነው አንዱ ግባችን የያ ትውልድ መረጃ ማሰባሰቢያ ሐውልታችሁ በአዲስ መልክ ተደራጅቶና ተዘጋጅቶ ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዛሬው ዕለት ተለቋል።

ያ ትውልድ ድረ ገጽ፦ www.yatewlid.com, www.yatewlid.org, www.ThatGeneration.org

በመቶ ሺህ የሚቆጠር ቤተሰብ ሕይወት የቀጠፈው የደርግና ተባባሪዎቹ ቤት ለቤት አሰሳ፣ ነፃ እርምጃና ቀይ ሽብር ሰማዕታት ሐውልት "ያ ትውልድ ድረ ገጽ" አማርኛና እንግሊዘኛን በማጣመርና አደራደሩን በማሻሻል ተዘጋጅቷል። ያ ትውልድን ማዕከል ያደረገው ይህ ድረ ገጽ ከጥንት ነገሥታቶቻችን ታሪክ በመጠኑ አካቶ በቀጣይነትም ያሉ የኢትዮጵያን የትግል ታሪክ እንዲያካትት ተደርጎ ተዘጋጅቷል።

የደርግ እና የኢትዮጵያ ማርክሲስት ሌኒንስት ድርጅቶች ህብረት (ኢማሌድህ) በሚል ከደርግ ጎን የተሰለፉት ጣምራ ድርጅቶች በትር፤ ቀይ ሽብር በርካታ ሊተኩ የማይችሉ የሀገሪቷን ወጣቶችን ጨምሮ የተማሩ ዜጎቿን አውድሟል።

በዚህ የደርግና ስብስቡ የጅምላ ፍጅት ተገለው የት እንደተጣሉ የማይታወቁ አሞራና ጅብ የቀበሯቸው ወጣቶች ስምና የተገኙትን ምስል ያካተተው ዋናው የቀይ ሽብር ሰማዕታት ገጽ መታሰቢያ ሐውልታችሁ አድርገናል። ይህ ክፍል ከ1983 ዓ.ም. በፊት በነበሩት በተለይ በዓፄ ኃይለሥላሴ ዘመን ያለውን የኢትዮጵያ 14 ጠቅላይ ግዛት ተመርኩዞ በያንዳንዱ ጠቅላይ ግዛት/ክፍለ ሀገር የተካተቱትን አውራጃና ወረዳ ምርኩዝ አድርጎ ተዘጋጅቷል። በአዲስ አበባ ከተማም በወቅቱ በደርግ ዘመን በነበሩት 25 ከፍተኞች መሠረት የተዋቀረ ነው።

በታሪክ ማሰባሰቡ ሂደት የዚህ ድረ ገጽ ሌላው ክፍል የደርግና ተባባሪዎቹ ቀይ ሽብር ተሳታፊዎች ገጽ ነው። በዚህም መደርደሪያ በየክፍላተ ሀገሩ፣ አውራጃ፣ ወረዳና ቀበሌ የነበሩ የቀይ ሽብር ኮሚቴ አባላትን ጨምሮ የማሰቃየቱ ቀጥተኛ ተሳታፊዎች የስም ዝርዝር ተካቷል።

የያ ትውልድ ድረ ገጽ የኢትዮጵያ ትግል ታሪክና መረጃ ማሰባሰቢያ ተንቀሳቃሽ ቤተ መረጃ እንደመሆኑ መጠንና መረጃን ደግሞ የሚፈልጉትን ብቻ እየመረጡ የሚከቱበት አይደለም ብለን እናምናለን። እኛ የነበረውንና የተደረገውን በመረጃ መልክ እናስቀምጣለን ለወደፊት ፀሐፊዎች፣ ለትምህርት፣ ስለ ታሪኩ ተመራማሪዎች፣ በጥቅሉ ለትውልድ። የሚፈለገው መረጃ በቀላሉና በነፃ ይገኝ ዘንድ። ይህን መረጃ የተጠቀሙና ስለ ሰው ልጅ እልቂት ህሊና ያላቸው ሁሉ ያን ትውልድ ሲጠቅሱ፣ ሲያስታውሱ ይኖራሉና።

በመሆኑም በዚህ ድረ ገጽ ሙሉ በሙሉ ባይሟሉም በደርግና ተባባሪዎቹ በኩል የሚኖሩ የጽሁፍም ሆነ ሌላ መረጃ በማሰባሰብ ድረ ገጹ ውስጥ እንዲካተት ለምትተባበሩ መደርደሪያው ዝግጁ መሆኑን እንገልጻለን።

ታሪክ ነውና፣ ተደርጓልና፣ በኢትዮጵያ ሕዝባዊ አብዮታዊ ፓርቲ (ኢሕአፓ) ከ1969/1970 ዓ.ም. እርምጃ የተወሰደባቸው የደርግና ኢማሌድህ አባላት፣ ካድሬዎችና ሌሎች ስም ዝርዝር የተገኘው ከነምስላቸው በዚህ ድረ ገጽ ተካቷል።

በያ ትውልድ ድረ ገጽ በተለይ ስለ ያ ትውልድ የተጻፉ መጻሕፍትን ዝርዝር ለማካተት ተሞክሯል። በመረጃ እጥረት ያልተካተቱ ወደፊት ሲሟሉ በዚህም ክፍል የቀይ ሽብር ፖሊሲ አውጭዎችና ዋና ቁንጮዎች መጽሐፍ ሳይቀር ተካቷል። መረጃ ነውና።

ያ ትውልድ ድረ ገጽ የኢሕአፓን "ዴሞክራሲያ" ዕትሞች ከቅጽ 1 ቁጥር 1 ጀምሮ እስከዛሬ ያሉትን ሲያካትት በወቅቱ በድርጅቱ ይወጡ የነበሩ ሌሎችም ተካተዋል። የመኢሶን "የሠፊው ሕዝብ ድምጽ" ልሳን በእጃችን ያለው ሲካተት የሌሎችም እስከተገኘ ድረስ ለመደርደር መደርደሪያው ተሠርቷል።

በሌላ በኩል በ50 ዓመት የኢትዮጵያ የፍትህና የዴሞክራሲ ትግል በኅብረ ብሔር ስምም ሆነ በዘር የተደራጁ የፖለቲካ ድርጅቶች ፕሮግራም፣ አጀማመርና ሌላም ለማካተት በተዘረጋው ክፍል የመረጃ መሰባሰብ ጠቀሜታውን የሚረዱና ትብብራቸውን በሚያሳዩ የየድርጅቶቹና ሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች ጥረት ይሟላል ብለን ተስፋ እናደርጋለን።

በሜይ ዴይ 2004 ለሕዝብ ይፋ የሆነው ያ ትውልድ ድረ ገጽ በዚህኛው አዲስና ተሻሽሎ በተለቀቀው ድረ ገጽ "That Generation" በሚል የእንግሊዘኛ ክፍል ተካቶለታል። የ«ያ ትውልድ ተቋም» ዓላማ፣ ተልዕኮና ራዕይ በተለይ በውጭው ዓለም ላሉና ላደጉ የኢትዮጵያ ልጆች ግንዛቤ ይሰጥ ዘንድ፣ በተጨማሪም ለተለያዩ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ተሟጋቾችና ሌሎች ድርጅቶች እንዲሁም መንግስታት በሀገራችን የተደረገውን አስከፊ ዘመነ ቀይ ሽብር የጥፋት ዘመን ግንዛቤ እንዲሰጥና ምን ተደርጎ እንደነበር ለማሳየት ጠቀሜታው የጎላ ነው። በዚህ ክፍል እስካሁን ያካተትናቸው ወደ 8000 የሚጠጉ የቀይ ሽብር ሰማዕታትን ወደ 1500 የሚጠጉ የቀይ ሽብር ተሳታፊዎች ስም ዝርዝር ሙሉ በሙሉ በእንግሊዘኛ ክፍሉ ተካታዋል።

የሀገራችንን የዴሞክራሲና የነፃነት የትግል ታሪክ ማሰባሰብና በተጀመረው ያ ትውልድ ድረ ገጽ መልሶ ለሕዝብ ማቅረብ ተልዕኮው አድርጎ የተነሳው «ያ ትውልድ ተቋም» በድረ ገጹ የተካተቱትን በመመልከት በኢሜል አድራሻችን (yatewld@gmail.com) ወይም በመደወል አስተያየታችሁን ትሰጡን ዘንድ በትህትናና በአክብሮት እንጠይቃለን። ያለውን የመረጃ ክፍተት በጋራ እናሟላ እንላለን።

«ያ ትውልድ ተቋም» በቀጣይነት በአለው አቅም መሠረት ተልዕኮውን እየተወጣ ይገኛል። አሁንም ወደፊትም የተለያዩ የያ ትውልድና ተዛማጅ መረጃዎች ያሏችሁ በመላክ ትተባበሩን ዘንድ በአክብሮት እየጠየቅን ድረ ገጹ አሁንም መሟላት ያለባቸው በርካታ ክፍተቶች አሉትና ለማሟላት ተባበሩን ስንል በያ ትውልድ ሰማዕታት ስም ጥሪያችንን እናቀርባለን።

***ምስጋና***

- የኢሕአፓ ዴሞክራሲያ ዕትሞችንና ሌሎች መጣጥፎችን እናገኝ ዘንድ ለተባበራችሁን የያ ትውልድ ወገኖች የከበረ ምስጋናችን በዚህ አጋጣሚ ይድረሳችሁ እንላለን።
- የቀይ ሽብር ሰማዕታት ወገኖቻችንን ስም ዝርዝርና የተገኘውን ፎቶ በማጣራት ለምትልኩልን ተባባሪ ወገኖች፤ ሙታን ወገኖቻችንን ከፍ ከፍ አርጋችኋልና በስማቸው ምስጋናችንን ተቀበሉን።

- «ያ ትውልድ ተቋም»ን በተለያየ መልኩ እየረዳችሁ ላላችሁ ወንድምና እህቶቻችን ከበሬታችን የላቀ ነው። አሁንም በማንኛውም መንገድ «ያ ትውልድ ተቋም»ን ለመተባበርና ለመርዳት ፍላጎት ላላችሁ ኢሜል (yatewlid@gmail.com) አርጉልን፣ ደውሉልን፤ የገንዘብ ድጋፍ ለማድረግ ፍላጐቱ ላላችሁ በድረ ገፃችን ላይ የተቀመጠውን የ PayPal Account በመጠቀም መርዳት እንደምትችሉ በዚህ አጋጣሚ ማሳወቅ እንወዳለን።
- በተቋም ደረጃ በሰሜን አሜሪካ ዋሽንግተን ዲሲ፤ ኮንግረስ ቤተመጽሐፍት እና በኢትዮጵያ የቀይ ሽብር ሰማዕታት መታሰቢያ ሙዝየምን ለምታደርጉልን ትብብር እጅጉን እናመሰግናለን።

የያ ትውልድን አኩሪ ታሪክ ለትውልድ ለማስተላለፍ ሁላችንም እንተባበር።

<<ያ ትውልድ ተቋም>> ለያ ትውልድ መታሰቢያነት።

ያ ትውልድ ተቋም

የካቲት 19 ቀን 2010 ዓ.ም. (February 26, 2018)

Email : yatewlid@yahoo.com, yatewlid@gmail.com,

ስልክ ፡ (703) 300 4302 ወይም (615) 306 4164

website : http://www.yatewlid.com , http://www.yatewlid.org